# የዘረኛነት አገልጋይ በመሆን የሚገኝ የዘለቄታ ጥቅም አይኖርም

የግንቦት 7 ድምጽ ቁጥር 59 ርዕሰ አንቀጽ

የግለሰብ ባህርይ እና ችሎታ የሚወሰነው በዘሩ፣ በብሄሩ፣ በጎሳው ወይም አባል በሆነበት ማኅበር ነው ብሎ የሚያምን አስተሳሰብ ‹‹ዘረኝነት›› በመባል ይታወቃል። ዘረኝንት ሰዎችን በቡድን ካልሆነ በስተቀር በግል አያውቃቸውም። ይህ አገርንና ሕዝብን የሚጎዳ ኋላቀር አስተሳሰብ አንድ ቡድን በሃብትና ሥልጣን የበላይነትን የሚይዝበት አድሎዓዊ ሥርዓት ይዘረጋል።

እ.ኤ.አ 1965 ወጥቶ ከ1969 ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለው የተባበሩት መንግሥታት *የሁሉም ዓይነት የዘር-መድልዖዎች ማስወገጃ ኮንቬንሽን* ‹‹*የዘር-መድልዎ*››ን በሚከተለው አኳኋን ይተረጉመዋል።

*የዘር-መድልዎ ‹‹….ዓላማው ወይም ውጤቱ ሰብዓዊ መብቶችንና መሠረታዊ ነፃነቶችን በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ፣ በባህላዊ ወይም በሌላ ማናቸውም የማኅበራዊ ሕይወት ዘርፍ ውስጥ በእኩል መጠቀምን የሚያጠፋ ወይም የሚያሰናክል በዘር፣ በቀለም፣ በአስተሳሰብ፣ በብሄር ወይም በጎሳ መነሻነት የሚደረግ አድልዖ፣ ማግለል፣ መከልከል ወይም የተለየ አሰራርን መጠቀም ነው።››*

ይህን ትርጓሜ የሚያሟላ የዘር-መድልዎ አገራችን ውስጥ ስለመኖሩ የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንጠቅሳለን።

1. የአገሪቱ የመከላከያ ሠራዊትና የስለላ ድርጅት ቁልፍ የአዛዥነት ቦታዎች ሙሉ በሙሉ ማለት በሚያስችል ሁኔታ በትግራይ ዘውጌ ማኅበረሰብ አባላት መያዛቸው ሃቅ ነው፡፡ በፌደራል የመንግሥት መዋቅርና ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ባላቸው እንደ ቴሌኮሚኒኬሽን፣ የመንገድ ሥራዎች ድርጅት፣ የሲቪል አቪየሽን፣ የኤሌክትሪክና መብራት ኃይል፣ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ባለሥልጣን መ/ቤቶችና ኮርፖሬሽኖች ቁልፍ የኃላፊት ቦታዎች በአንፃራዊ ስሌት ባብዛኛው በትግራይ ዘውጌ ማኅበረሰብ አባላት ተይዘዋል። በፌደራልም አገዛዙ ውስጥም ዝቅተኛ የክፍል ኃላፊነት የሥራ መደቦች እንኳን ሳይቀር በዘር በመጠቃቀም በርካታ የኃላፊነት ቦታዎች የተያዙት በትግራይ ተወላጆች ነው። ይህ የፌደራል መንግስቱን የሥራ ዘርፎች በትግራይ ተወላጆች የማስያዝ መርሃ ግብር  በትግራይ ክልል በ1997 ዓ.ም በተደረገ ጥናት በአስር ዓመት ውስጥ በእዚህ ክልል ሊፈጠር የሚችለውን 500000 የሥራ አጥ ቁጥር ለመቀነስ የተዘጋጀው የፖሊሲ ውሳኔ ውጤት ነው።

2. ኢኮኖሚው በተመለከተም እንደ ኮንስትራክሽን፣ ሪል እስቴት፣ ፋይናንስ፣ ትራንስፖርት፣ የውጭ ንግድና የትራንዚት አገልግሎት የመሳሰሉት በተለይ ዘመናዊ የሆነው ዘርፍ በአብዛኛው በትግራይ ዘውጌ ማኅበረሰብ አባላት የቀጥታና የእጅ አዙር ቁጥጥር ሥር ወድቀዋል። በዚህም ምክንያት ወይ የወያኔ አሊያም ከትግራይ ዘውጌ

ቡድን ያልሆኑ ኢትዮጵያውያን በአገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ የመሳተፍ ነፃነታቸው በእጅጉ ተሸመድምዷል።

3. የኢትዮጵያ ሲቢል ማኅበረሰብ ያለበት ሁኔታም ተመሳሳይ ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሙያና ሕዝባዊ ማኅበራት አመራር አባላት በተጠና ሁኔታ ለወያኔ ቅርበት ላላቸው የትግራይ ተወጆች አሊያም በዘራቸው የትግራይ ተወላጆች በሆኑ ሰዎች እየተያዙ ነው። ከሁለቱም ያልሆኑ ኢትዮጵያዊያን የወያኔ ሎሌዎች እስካልሆኑ የመረዳጃ ማኅበር እንኳን ማቋቋምና መምራት እንዳይችሉ ተደርገዋል።

ከላይ እንደተገፀው የተባበሩት መንግሥታት ባስቀመጠው ትርጓሜ መሠረት የዘር መድልዎ የሚፈፀመው ዘርን ወይም አስተሳሰብን መሠረት አድርጎ ሊሆን ይችላል። ዛሬ በአገራችን ሁለቱንም መሠረት ያደረገ የዘር መድልዎ እየተደረገ ነው። የዚህ መድልዎ ተጠቃሚዎች የትግራይ ዘውግ ማኅበረሰብና ለወያኔ ገዥዎች ስብዕናቸው የሸጡ ጥቂት የወያኔ አገልጋዮች ሲሆኑ ተጠቂው ግን በቁጥር እጅግ ብዙ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው።

እንዴት ነው ይህንን አስከፊ የዘር መድልዎ መዋጋት ያለብን የሚለው ጥያቄ መሠረታዊና አንገብጋቢ ነው። ይህንን ጥያቄ ስንመልስ፤

1. በረዥም ጊዜ ስሌት ከታየ ከዘር-መድልዎ ተጠቃሚ የለም - ሁሉም ተጎጂ ነው። ለጊዜው እየተጠቀሙ ያሉት ወገኖችም ከአጭር ወደ ረዥም የጊዜ ስሌት ሲሸጋገሩ አሁን እየጠቀማቸው ያለው ሥርዓት በረዥም ጊዜ አጥፊዓቸው እንደሆነ ይረዱታል።
2. በማናቸውም የዘርመድልዎ እንደታየው ሁሉ የመድልዎው ተጠቃሚ የሆነው ወገን አባላት በሙሉ ተጠቃሚ አይሆኑም። አብዛኛውን ጊዜ የተጠቃሚው ቡድን በአብላጫው አባላት ስም ይነገዳል እንጂ አብዛኛዎቹ ከፍርፋሪ የበለጠ ጥቅም አያገኙም።
3. የዘር መድልዎን ለማጥፋት የሚደረግ ትግል አላስፈላጊ ወደ ሆኑ ጽንፎች እንዳይሄድና አሰቃቂ መዘዞች እንዳያስከትል ከመድልዎው ተጠቃሚ የሆኑ ወገኖች የሆኑ የሥርዓቱን ኢፍትሃዊነትና ኢሰብዓዊነት ተቃውምው ‹‹በስማችን ይህ ግፍ ሲፈጸም ዝም ብለን አናይም›› ማለት ይገባቸዋል። የደቡብ አፍሪካን አፓርታይድ ለማስወገድ የሥርአቱን ግፈኛነት ተቃውመው የታገሉ ነጭ ደቡብ አፍሪካዉያን ሚና ምን ያህል ከፍተኛ እንደነበር ልብ ይሏል። እኛም ከትግራይ ተወላጆች ተመሳሳይ ነገር እንጠብቃለን።

በዚህ አጋጣሚ ዘረኛውን አገዛዝ ለመፋለም ቆርጠው ለተነሱ የትግራይ ተወላጆች እና የዘረኛው የመለስ ዜናዊ መሳሪያ በመሆን በወገናቸውን ላይ ለደረሰው የዘር ውርደትና ዘረኛ ዘረፋ ተጠያቂ ነን በሚል ቁጭት ወያኔን አምረው ለመታገል ለተነሱት የብአዴን የኦህዴድና የሌሎችም ድርጅቶች የቀድሞ የኢህአዴግ አባላት ያለንን አክብሮት እንገልፃለን፤ ሌሎችም አርዓያነታቸው እንዲከተሉ እናበረታታለን።

ግፍ የሚወልደውን አመፅ መቆጣጠር የማይቻልበት ሁኔታ ላይ ሊደረስ ይችላል።
መለስ ዜናዊና ዘርፊው፣ ግፍ ሰርተውና ደም አፍሰው የማይጠግቡ ጓደኞቹ የገነቡት ዘረኛና አድልዎአዊ ሥርዓት በላያችሁ ላይ መፍረሱ አይቀርም። ከዚህ የግፍ ሥርዓት ጋር በዘር ይሁን በጥቅም የተሳሰሩ ወገኖቻችን የመለስ አደገኛ አካሄድ በሃገራችንና በሁላችንም ላይ እንዲያጠላ ያደረገው የጨለማ ደመና ያረገዘው የመከራ ዶፍ ለማስቆም ቆርጠው ሊነሱ የሚገባበት ሰዓት አሁን ነው። ይህንን ብካይ አምራች የሆነን ዘረኛ ሥርዓት አፈራርሰን ፍትህ የሰፈነባት፤ ልጆቻችን ተፋቅረው የሚኖሩባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የምናደርገውን ትግል በዘር ሥልጣን የተሰጣቸው የወያኔ ጄነራሎችና የስለላ ድርጅቱ መኮንኖች ሊገቱት አይችሉም። ትግሉ እየከረረ ሲመጣ መለስና በመለስ አገልጋይነታቸው

የብዙ ሚሊዮኖች ዶላር ጌቶች የሆኑት ጀኔራሎች በየፈረንጅ ሃገሩ ያስቀመጡትን ገንዘብ እያጣጣሙ ለማርጀት ባገኑት ቀዳዳ ሁሉ ሃገር ጥለው መሸሻቸው አይቀርም። የአምባገነኖች የጀግንነት ጉራ መጨረሻው ይህ እንደሆነ ከቅርቡ ታሪካችን አይተነዋል። ሕዝብ ግን በክፉም በበጎም አብሮ ከመኖር ሌላ አማራጭ የለውም። ይህን መረዳቱ፤ ተረድቶም ለዘላቂው ማምለጫ ለሌለው የጋራ ህይወት ሕዝብ በዘርና በአምባ-ገነኖች የማጭበርበሪያ ፕሮፓጋንዳ ሳይታለል በአንድነት ሊቆም ይገባዋል።

ይህ የጋራና የአንድነት የትግል ጥሪ መለስ ዜናዊ የዘረኛና የዘረፋ ሥርአቱ መከላከያ አድርጎ ከሌላው ወገኑ ጋር ሊያጋጨው የሚፈልገውን የትግራይ ወገናችንን ይመለከታል። ምኞታችን የዚህን ታሪካዊ ጥሪ ክብደት በመረዳት የትግራይ ምሁራንና ህዝብ ምላሹን ይሰጣሉ የሚል ነው።

http://www.ginbot7.org/News_Paper/Ginbot_7_Dimts_Issue_No59.pdf